# ዝም ማለት ወንጀል ሆነብኝ።

*መስከረም ፲፩ ቀን ፳፻፮ ዓመተ ምህረት*
*አንዱ ዓለም ተፈራ የእስከመቼ አዘጋጅ*

***" 'የወያኔን መንግሥት ማስወገድ ዋነኛው አጀንዳዬ ነው።' የሚለው ግንቦት ሰባት የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ በኤርትራ ምድር እንደሚንቀሳቀስና ከኤርትራ መንግሥትም እገዛ እንደሚያገኝ አስታወቀ።"*** *በሚል ርዕስ፤ ሁለቱ የግንቦት ሰባት ከፍተኛ አመራር አባላት፤ ዶክተር ብርሃኑ ነጋና አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ተናጋሪዎች፤ ሶስተኛው አመራር አባል፤ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ አስተናጋጅ የሆኑበትን ዘገባ፤ ዛሬ መስከረም ፲፩ ቀን ፳፻፮ ዓመተ ምህረት በአሜሪካ ሬዲዮ ቀረቦ ደጋግሜ አዳመጥኩት። እስከዛሬ በተለያዩ ቦታዎች ባደረጓቸው ንግግሮች የተከታተልኳቸው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፤* ***"ግንቦት ሰባት፤ ሥልጣን ለመያዝ፤ መዋቅር፣ መርኀ ግብርና ፍላጎት የሌለው እንቅስቃሴ ነው። ፓርቲ አይደለንም። ብዙዎችን የተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ያካተተ መድረክ ነው።"*** *ያሏቸውን ሳክልበት፤ ግራ የሚያጋባ ሂደት ስለተመከትኩ፣ <u>ዝም ማለቱ ወንጀል ሆኖብኛል።</u> እናም ይቼን ጭሬያለሁ።*

*ዶክተር ብርሃኑ ነጋን ሳዳምጥ፤ እኔ አሁን የማደርገው፤ ሀገር እንዳይኖረኝ ያደረገኝን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት መታገልና መጣል ነው። ከዚያም የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጠው መንግሥት እንዲኖር ነው የምፈልገው። ግንቦት ሰባት የውጭ ጉዳይ፣ የትምህርትና የኤኮኖሚ መርኀ ግብር የለውም ብለዋል። እንቅስቃሴ ነው የያዝኩት በማለት አስረግጠው፤ እምኑኝ ግዴላችሁምን ጨምረውበታል። በሌላ በኩል ደግሞ* ***"ግንቦት ሰባት የሕቡዕ ድርጅት ነው። ብዙውን ግልፅ ሊያደርግ አይችልም።"*** *ሲሉ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አዳምጫቸዋለሁ። እንዴት ያለ ነገር ነው?*

*ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፤* ***"ሰላማዊ"*** *የሚባለውን ትግል እስከመጨረሻው ሄጀበታለሁ። ለኔ ይኼን ለመንገር መሞከር፤ ላሳር ነው። አይገባኝም። በማለት የሰላም ትግሉን የመጨረሻ ሞት ነግረውናል። እንዲያውም እንደነሱ እልህ እንድንገባና ለዴሞክራሲ የምናደርገውን ትግል በነሱ የእልህ ደረጃ ማሳደግ እንዳለብን ነግረውናል። የትግል ጥረታችን ማደግ እንዳለበት ያደረጉት ገለፃ ትክክለኛና የምጋራው ቢሆንም፤ ስለሰላማዊ ትግል ያላቸው ግንዛቤ ግን ከመሠረቱ ትልቅ ጥያቄ እንዳስቀምጥበት አድርጎኛል። ይኼን በሚመለከት በሠፊው በኋላ እመለስበታለሁ። ከዚህ አስከትለው፤ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት በአመፅ መወገድ እንዳለበት አማራጭ የሌለው መሆኑን አስምረው፤ በአካባቢው ያሉት ሀገሮች በሙሉ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ተባባሪዎች መሆናቸውንና የኤርትራው መንግሥት ብቻ አማራጫቸው እንደሆነ ነገሩን። እንደሳቸው ገለፃ፤ ይህ የአማራጭ ማጣት ወደ አስመራ እንዳስሮጣቸው ደጋግመው አስምረውበታል። በዚህ ጉዳይ ላይም ዝቅ ብዬ እመለስበታለሁ። ለጥቀውም፤ የቆምነው ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱ የመረጠው መንግሥት እንዲያቋቁም እጥራለሁ ብለዋል።*

*የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥትን ለመጣል መታገል ነው የያዝኩት እያሉ፤ የትጥቅ ትግል ለማድረግ የመንቀሳቀሻ ቦታና ድጋፍ ከኤርትራ መንግሥት እያገኘን ነው እያሉ፤ ከኤርትራው መሪ ጋር በተደጋጋሚ በብዙ ርዕሶች ተነጋግረናል እያሉ፣ ሰላማዊ ትግሉ አይሠራም፣ በአመፅ ነው መወገድ ያለበት እያሉ፤ መርኀ ግብር የሌለን፣ ፓርቲ ያልሆን፣ እንቅስቃሴ ነን ማለት ምን ማለት ነው? ይህ የኔ አንዱ መሠረታዊ ጥያቄዬ ነው። ግንቦት ሰባት ታግሎና ድል አድርጎ ሥልጣኑን ለሕዝቡ ሲያስረክብ ማየት ስለቸገረኝ! እንዴት ያለ አሠራርና መዋቅር እንደሚያስተናግደው አልታይህ እያለኝ።*

*ዶክተር ብርሃኑ ነጋ አንድ የጠቆሙን ቁም ነገር አለ።* ***"የወያኔው መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ፤ የኤርትራ መንግሥት ተቃዋሚዎችን ማንቀሳቀሱ ርባና የለውም። አይሳካለትም። ነቅነቅ ማለት ያልቻለ ተቃዋሚ ነው።"*** *ብለውናል። ይኼን በኤርትራ ኢሳያስ አፈወርቂ ከሰበሰባቸው ተቃዋሚዎች የተለዬ የሚያደርገው ምን እንደሆነ ማየት አሁንም ተስኖኛል!*

*የኤርትራን መሪና በኤርትራ ያለውን የፖለቲካ ጉዳይ አስመልክቶ፤ ዶርተር ብርሃኑም ሆኑ በተለይም አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፤ በኤርትራ ያለው የዴሞክራሲያ ሁኔታም ሆነ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ የኛ የእንቅስቃሴያችን ደጋፊዎች መለኪያዎች አይደሉም። የኤርትራን መንግሥት አንገመግምም። የኤርትራ ፖለቲካ የኛ ጉዳይ አይደለም። ማለትም በኔ ትርጉም፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በታሪክ ስለነበራት፣ አሁን ስላላትና ለወደፊቱ ስለሚኖራት ትስስር የኛ ጉዳይ አይደለም። ኤርትራ በኛ ውስጥ ልዩ ቦታ ያላት ሀገር አይደለችም፤ እንደማንኛውም ሀገር የራሷ ጉዳይ የራሷ ነው። የኢሳያስ አፈወርቂ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ለኛ ጉዳያችን አይደለም። የኢሳያስ አፈወርቂ በኤርትራ ሕዝብ ላይ የሚያደርሰው በደል የራሳቸው ጉዳይ ነው ማለታቸው ነው። እንግዲህ የኢሳያስ መንግሥት ጠበቃ ከመሆንና በሱ ትዕዛዝ ለማደር ከማጎንበስ ሌላ ምን ሊባል*

እንደሚችል እናንተው ፍረዱ! ለካስ ከንቱ ድካም ነው በሎንደን፣ በፓሪስ፣ በዋሺንግተንና በሮም መንግሥታቶችን ድጋፍ ለወያኔ አትሥጡ እያልን የምንደክመው። በአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ የፖለቲካ ዕውቀትና ግንዛቤ ስሌት፤ እነሱ የሚከተሉት የፖለቲካ ዘዴያቸው፤ የራሳቸው እንጂ የኛ ጉዳይ አይደለምና!

በአሁን ሰዓት፤ የጊዜያዊ ጥቅም ለማግኘት ብለን፤ የኋላ ኋላ የወደፊት መጪ ትውልዶችን የሚጎዳ አቋም መውሰድና በሥራ ላይ ማዋል፤ አድርባይነት ነው። በቁም ነገር አቋም ብለን የምንወስደው፤ መሠረታዊ እምነታችን የተተከለበት ዕሴት መሆን አለበት። የዕለቱን እውነታ ተከትሎ የሚተጣጠፍ አቋም ከሆነ፤ አድርባይነት ነው። ለአቋማችን የስኬት መንገድ በመፈለግ በኩል አጫጭር ጊዜያዊ ስልቶች እናበጃለን። እነዚህ ስልቶች፤ የወቅቱን ሁኔታ ከዘለቄታው ግብ አቋማችን አኳያ ጠቃሚ መንገዶችን በመመርመር የምንጠቀምባቸው ይሆናል። በአኳያው ደግሞ፤ እኛ የራሳችንን ስናስብ፤ በጊዜያዊ ስልታችን ያካተትናቸው ክፍሎችም፤ የራሳቸውን ጥቅም አስጠባቂ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። ኢሳያስ አፈወርቂ የኢትዮጵያ ዋና ጠላት ነው። ከርሱ ጋር የሚደረግ ማንኛውም ትብብር ለኛ ከሚያስገኝልን ጥቅም አንፃር፤ የርሱም ተጠቃሚነት እንዳለ መዘንጋት የለብንም፤ በሀገሩ ውስጥም ሆነ በኢትዮጵያ የነገ ሕልውና ላይ! የርሱ ጥቅም ከዘለቄታው ኢትዮጵያን ከማፈራረስና ከማዳከም አኳያ የመነጨ ነው። አሁን፤ **“ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የዛሬ ሃምሳ ዓመት የተፈጠረች ናት።”** የሚለው ኢሳያስ፤ ምን አስልቶ ነው ከኛ ጋር የሚተባበረው? ብሎ መጠየቅ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው። የኛ ጥቅም ደግሞ በብዙ መንገድ ከኤርትራውያን ወገናችን ጥቅም ጋር የተያያዘ ነው። የኢሳያስ አፈወርቂ ጥቅም ከኤርትራዊያን ወገኖቻችን ጥቅም በተቃራኒ የቆመ ለመሆኑ፤ በመካከላችን ብዥታ ያለው የለም። በነሱ ጉሮሮ ላይ ችካል ስንቅረን የኛን ግብ እንመታለን የሚለው ከቁንፅልነቱ ባሻገር፤ አረመኔነት ነው። **“አሜሪካ ታደርገዋለች።”** የሚለውም፤ ደካማ አስተሳሰብን ያመለክታል።

ሰላማዊ ትግል በመሠረቱ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሀገር፤ እስከዛሬ የነበረና ባሁኑ ሰዓትም ያለ እንቅስቃሴ ነው። ሰላማዊ ትግል የምርጫ ጉዳይ አይደለም። ሰላማዊ ትግል ከትንሽ ጉዳይ አንስቶ እስከከፍተኛ ሀገራዊ ጉዳይ ድረስ፤ ለኑሮ እንቅፋት ሲገጥም፤ የሚሠለፉበት የትግል ዘዴ ነው። በሰላማዊ ትግል የመንግሥትን መለወጥ ብቻ ሳይሆን፤ ከዚያ በመለስ ያሉ ጉዳዮችን ለማስፈፀምም፤ እምቢተኛ ከሆነ የመንግሥት መዋቅርም ሆነ የግል ባለንብረቶች ጋር የሚደረግ ትግል ነው። ተማሪዎች ምግባችን ጎደለ ብለው ትምህርት ሲያቆሙ ሰላማዊ ትግል ነው። ሠራተኞች ደምወዝ አነሰን ይጨመርልን ብለው ሥራ የማቆም አድማ ሲያደርጉ፤ ሰላማዊ ትግል ነው። እናም ባጭሩ ሰላማዊ ትግሉ፤ በተጨባጩ የቦታው እውነታ ተመሥርቶ የሚካሄድ ትግል ነው። እንዲያውም አሁን ላለንበት የፖለቲካ እውነታ የሰላማዊ ትግሉን ጠቀሜታ አለመረዳታችንን የዶክተር ብርሃኑ ነጋ አገላለፅ አስምሮ አሳይቶናል።

የያዝነው ትግል እንዳይሳካ ያልሆነበት አንዱ ምክንያት፤ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በትክክል እንደገለፁት የኛ ድክመት እንጂ፤ የወያኔ ጥንካሬ አይደለም። የኛ ድክመት ደግሞ በጃችን ያለውን የትግል ዕድል በደንብ አለመጠቀማችን ነው እላለሁ። ይህ ደግሞ የሰላማዊ ትግሉን ሆነ የትጥቅ ትግሉን አይሠርዝም። የሰላማዊ ትግሉ፤ የትጥቅ ትግል ኖረም አልኖረም ምን ጊዜም አይቀሬ መሆኑን ለማስረገጥ እፈልጋለሁ። ትልቁ ድክመታችን፤ የሰላማዊ ትግል ስንል፤ ዕለት በዕለት በየቦታው የሚደረገውን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት በደል፤ በየተገለፀበት ቦታ፣ ወቅትና ሁኔታ መቃወም አለመቻላችን ነው። በአንድ ትምህርት ቤት በተማሪዎች ላይ የሚደረገውን በደል፤ በመቃወም መምራት መቻል፣ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚደረግን አድልዖ በመቃወም መምራት መቻል፣ በነጋዴዎች፣ በእስልምና ተከታዮች፣ በመምህራን፣ በክርስትና ተለታዮች፣ በአማራዎች፣ በአኙዋኮች፣ በኦሮሞዎች፣ በሶማሌዎች ላይ የሚደረጉ በደሎችን፤ በቦታውና በሰዓቱ በመገኘት ተቃውሞውን መምራት አለመቻላችን ነው። እነዚህ ናቸው ዋና የሰላማዊ ትግሉ መሠረቶች። ለየተጠቂዎች መተው ሳይሆን የአንዱ ሀገር አቀፍ ትግል አካል አድርገን አለመተባበራችን ድክመታችን ነው። ያለነዚህ ሰላማዊ ትግል የለም። ያለነዚህ የትጥቅ ትግል የለም። የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት እነዚህን በደሎች ካላደረገ ደግሞ፤ ሕይወት የለውም። ይህ ነው የማንነቱ መገለጫ። በትልቁ በመንግሥት ደረጃ የሚደረጉ በደሎች፤ የነዚህ ትንንሽ በደሎች ቁንጮ ነው። እነዚህ አከላቱ ናቸው። ያለነዚህ በደሎችና ተቃውሞዎች አጠቃላይ ትግል፤ ሰላማዊም ሆነ የትጥቅ ትግል የሚባል የለም። እናም እነዚህ በየተከሰቱበት ቦታ ተገኝቶ፤ ተቃውሞዎችን መምራት የቻለ፤ ትግሉን ወደፊት አራማጅ ነው። በየቀበሌው ተገኝቶ፤ የቀበሌውን ነዋሪ ወገናችንን በደል መካፈልና ለተቃውሞው አብሮ መሠለፍ፤ የትግሉ ዋና መሠረት ነው። ይህ የሰላማዊ ትግሉ ነው። ይህን ትቶ ጉዞ፤ የጨለማ ዳበሳ ነው። ይኼን እያደረጉ ያሉ የሰላማዊ ትግሉ ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው ትግሉ አምዶች ናቸው። እየተደረገም ካልሆነ፤ የትግል ሀ ሁ ቆጠራ ትምህርት ቤት መግባት አለብን። ከነዚህ ጥቃቅን ትግሎች

ተነጥሎ መንግሥት መቀየር አለበት ማለት፤ የፖለቲካ ምጥቀቱና ትምህርቱ ላላበሰለን እንደኔ ላለን ተራ ኢትዮጵያዊያን፤ ትርጉሙ የሕዋ ስነ ምርምር ያህል ሩቅና ውስብስብ ነው።

ትግሉ ደግሞ ወደፊት የሚሄደው እንደኔ ያለነው የፖለቲካ ትምህርቱና ምጥቀቱ ባላበሰለን ተራ ኢትዮጵያዊያን ስለሆነ፤ በኛ ደረጃ ሲቀርብ ነው ተሳትፏችን የሚያድገው። እናም የትግሉ መሽከርከሪት በሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ሕልው ውስጥ መነዳት አለበት። ይህ የሚሆነው ደግሞ፤ የሕዝቡን ኑሮ ትግሉ ሲያንፀባርቅ ነው። በተራቀቀ የትግል ትንታኔ ወይንም በሕዋ ላይ በሚንሳፈፉ የተሽሞነሞኑ የትግል መሥፈርቶች ላይ የተተከለ እንቅስቃሴ፤ አንቀሳቃሾች ነን በሚሉት መካከል ካለ ጉንጭ አልፋ የአእምሮ ግብግብ ከመሆን አልፎ፤ የትም አይደርስም። ሕይወት ኖሮት እንዲያድግና ግቡን እንዲመታ፤ በተጨባጭ ዕለት ተዕለት የሕዝቡ ኑሮና ወቅታዊ በደሎች መመርኮዝ አለበት። ይህን ደግሞ አብረው የሚኖሩ ናቸው የሚገነዘቡት፣ የሚመሩትና ወደፊት የሚወስዱት። ለዚህም ነው ሕዝባዊ ትግል ብለን አፋችንን ሞልተን መናገር የምንችለው።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ አሁን ዓለም ባለችበት የፖለቲካ እውነታ፤ የትናንቱ የትግል ዘዴ ቦታ የለውም። ይህ ማለት መሠረታዊ የሆነው የሰላማዊና የትጥቅ ትግል ዘዴ ቀረ ማለት አይደለም። ነገር ግን፤ የትጥቅ ትግል የሚለው ግንዛቤያችን መመርመር አለበት። አዎ አረመኔ አምባገነኖች የሚገባቸው ቋንቋ በትር ነው። አዎ አረመኔ አምባገነኖች ወደው ሥልጣን አይለቁም። ነገር ግን፤ በአሁኑ የዓለም የፖለቲካ እውነታ፤ በተለይም ዩናይትድ ስቴትስ ዓለምን **"የኔን አጀንዳ የግድ ተቀበሉ!"** በማለት <u>የአሸባሪዎችን ማሳደድ</u> ጉዳይ የዓለም ጉዳይ ባደረገችበት ወቅት፤ ከጎረቤት ሀገር ተነስቶ፤ ከገጠር ኃይሉን አጠናክሮ፣ አንዱን ብርጌድ አቸንፎ ሌላውን አስከትሎ፣ ወደ ማዕከላዊ የመንግሥት ቦታ መዝመት የሚለው መመርመር አለበት። በአኳያውም፤ በትናንት አጀንዳዎች የሚደረግ ትግል መመርመር አለበት። የዛሬው ትግል፤ ዛሬ ያለው መንግሥት ዛሬ በሚፈፅመው በደል ላይ የተመረኮዘ ነው። ትግሉ በትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥትና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ነው። ይህ ደግሞ የትግሉን ዘዴ ከጊዜው ጋር በሚሄድበት መንገድ ማስተካከል እንዳለበት ያመለክተናል።

በኔ ግምት፤ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌና አቶ ኤፍሬም ማዴቦ የያዙት፤ ድንገት የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ሲወድቅ፤ የተደራጀ ጦር ይዘን ብንገኝ፤ ሥልጣኑን የመውሰድ ወይንም የመደራደር ዕድላችን የሰፋ ነው ከሚል ስሌት የመነጨ ይመስለኛል። ለዚህ ደግሞ መጠለያ መፈለግ ግድ ስለሆነ፤ ወደ ኤርትራ መጓዛቸው ሕልም ፈቺ አይጠይቅም።

በርግጥ የትጥቅ አመፅ በአሁኑ ሰዓት ይጠቅማል። ይህ ግን ግድ የሚላቸው ጉዳዮች አሉ። አንደኛ፤ አንድ ብቻ የታጠቀ ሠራዊት የመኖሩ ግዴታ ነው። እንደ ፖለቲካ ፓርቲዎች ብዛት፤ እያንዳንዱ የራሱ የታጠቀ ሠራዊት ኖሮት፤ ሠልፉም ያንኑ ያህል ከሆነ፤ ቀሪው እግዚዖ! ማለት ብቻ ነው። ዩጎዝላቪያ ምስጋና ይግባው ማለታችን ይከተላል። ሶማሊያ በየት ተገኝቶ የምንልበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። አንድ የታጠቀ ጦር ብቻ እንዲኖር ከተስማማን ደግሞ፤ አንድ መሪ ድርጅት ብቻ እንዲኖር መቀበላችን ነው። አንድ መሪ ድርጅት ደግሞ፤ የሁሉንም አሰባሳቢ አንድ ራዕይና አንድ ግብ ብቻ ነው የሚያቀነቅነው። ይህ ደግሞ ሕዝባዊ የሆነ ጦርና፤ አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ያካተተ ድርጅት የመሆን ግዴታ አለበት። ታዲያ በዚህ ሂደት የትጥቅ አመፁ የሰላ ይሆናል፤ ድልና ፍጥነቱም አያጠያይቅም።

ይኼን የትጥቅ ትግል፤ የመቅናጠጫ ቦታ አማራጭ አጣሁ ብሎ ከአንበሳ አፍ ወደ ጅብ አፍ የምንሮጥበት ምርጫ ፍለጋ ድንብርብርነት የለም። ባሁኑ ሰዓት የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት በሕዝቡ ያልተወደደ ለመሆኑ ሁላችንም እንስማማለን። ታዲያ ሕዝብ ያልወደደው መንግሥት እንዴት አድርጎ ነው ሕዝቡን ሊቆጣጠር የሚችለው። ትግሉን በሕዝቡ ውስጥና በሀገሪቱ ውስጥ ለማካሄድ ምቹ ሁኔታ አለ። ትጥቁም ሆነ ምሽጉ ሕዝቡ ነው። ይኼን ሁኔታ ያገናዘበ የትግል መንገድ ቀይሶ መጓዝ እንችላለን። የግድ በትናንቱ የጦር ስልትና መንገድ መጓዝ የለብንም። የጎደለው ነገር፤ ትግሉን የሚያራምዱት ወገኖች፤ በእኔ ልምራ እኔ ልምራ ልክፍት ተጠምደው፤ ባንድነት ያልተነሱበት እውነታ መስፈኑ ነው። ትግሉ በሕዝቡ መካከል እስከተካሄደ ድረስ፤ አመፁ ሕዝቡ ባለባቸው ቦታዎች በሙሉ በተቀናጀና በተፋጠነ መንገድ ይካሄዳል። የመቅናጠጫ ቦታ ፍላጋ የሚኬድበት ዘመን ውስጥ አይደለም ያለነው። በሕዝብ ላይ እምነት የማሳደርና በሕዝቡ የመተማመን ጉዳይ ነው። አንድ አጀንዳና አንድ ትግል ብሎ የመነሳት ጉዳይ ነው። ሕዝቡ ይኼን የመሰለ መተባበርና አንድ ሀገራዊ አጀንዳ ያለው ትግል ሲያይ፤ ከድርጅቶችና ከመሪዎቻቸው ቀድሞ እንደሚሰለፍ የሚጠራጠር የለም። የትግሉ

መንገድ ያልተለመደና ካሁን በፊት ያልታዬ ሊሆን ይችላል። ይሁና! ጊዜው የሚጠይቀውና የሚፈቅደው እኮ ሁሌም አዲስ ነው። የሚያሰጋ ነገር የለም።

አስጊውስ ጉዳይ፤ ግንቦት ሰባት የራሱ ጦር፣ የኦጋዴን ነፃ አውጪ የራሱ ጦር፣ የኦሮሞ ነፃ አውጪ የራሱ ጦር፣ የአርበኞች ግንባር የራሱ ጦር፣ የትግራይ ታጋይ የራሱ ጦር፣ የሲዳማ ታጋይ የራሱ ጦር፣ የአኝዋክ ታጋይ የራሱ ጦር፣ የአማራ ታጋይ የራሱ ጦር፣ የአፋር ታጋይ የራሱ ጦር ይዞ፤ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት የወደቀ ዕለት ነው። ያኔ ምን ይሆናል? መላ ምቱበት።